# ኢህአዴግም እንክርዳድም መሆን አይቻልም!

አጬሌ (ከአሜሪካ ግቢ) 03-03-18

*“ስንቶች ተኮላሽተው ካረንቋ ዘቀጡ፣*

*ስንቶች ተቸንፈው ከጎዳና ወጡ፤*

*ጥቂቶች ቆራጦች ያልተንበረከክነው*

*ነግ እልፍ እንሆናለን ታሪክ ምስክር ነው።”* የሚለው የብአዴን/ኢህአዴግ የትግል መዝሙር በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ መፅደቅ ጉዳይ የግንባር ስጋ ሆነው የተገኙት፣ ጥቂት ሆነው እልፍ የሆኑትን ቆራጥ ታጋዮች ያስታውሳል። በአገር ትቀጥል አትቀጥል ጉዳይ ክህደት የፈፀሙት፣ ካረንቋ የዘቀጡትን ተኮላሾች ያስታውሳል። ሸሽተውና መጣሁ ብለው ከመድረኩ የጠፉት፣ ፈተናው ሲመጣ መስመሩና ጎዳናውን ጥለው ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ እብስ ብለው የጠፉትን ያስታውሰናል። እነሆ ወደ ፓርላማው…

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፀድቋል (አራት ነጥብ።) የአዋጁ መፅደቅ፣ እንዲፀድቅ ባስፈለገበት ምክንያት ማለትም የዜጎች ህይወትና ንብረት አደጋ ላይ የመውደቅ ጉዳይ፣ የሰላም እጦት ስጋት ጎልቶ መታየት፣ የህዝቦች የዛሬና የቀጣይ ሉዓላዊነት ጉዳይ ስጋት እያጋጠመው በመጣበት ጉዳይ ወዘተ… ሲታይ እጅግ አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን አማራጭ የሌለውም ነው። በሰላም መናኸሪያነቷና በአካባቢው አገራት የሰላም ምንጭነቷ በምትታወቀው አገራችን ለአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መታወጅ ምክንያት የሆነ አደጋ ማጋጠሙ ደግሞ እጅግ የሚያስቆጭም ነው።

በትናንቱ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማፅደቅ ጉዳይ በተፈጠረው አጀንዳ የሚዲያውም ሆነ የየሰዉ መነጋገሪያ የሆነው የ88ቱ “ የተከበሩ ምክር ቤት አባላት” ተቃውሞና የ7ቱ “የተከበሩ ምክር ቤት አባላት” ድምፀ ተዓቅቦ ነው። ጥሩ ነው። እንኳንስ የ95 ሰዎች ለኢህአዴግ ድምፅ ሊሰጡ ገብተው ከኢህአዴግ መስመር የመጥፋት ጉዳይ፣ የኃይማኖት ሰዎች እንደሚገልፁት፣ “ከ100ዎቹ በጎች የአንዲቷ በግ መጥፋት” ምን ያህል እንዳንገበገበ አንብበናል።

“አንድ ሰው መቶ በጎች ቢኖሩትና ከእነሱ ውስጥ አንዷ ተነጥላ ብትጠፋበት አንዷቷን ለመፈለግ 99ኙን በጎች ትቶ ይሄዳል…” እንዳሉት፣ 95ቱን የምክር ቤት አባላት፣ ሰዉና ሚዲያው፣ በተለይ ማህበራዊ ሚዲያው ከኢህአዴግ ድርሳን ውስጥ እያገላበጠ ከወዴት አላችሁ ብሎ መጠየቁ ኃጢዓት አይደለም።

ነገር ግን መጠየቅ ያለበት ሌላም ጉዳይ አለ። በምክር ቤቱ መገኘት እየተገባቸው ያልተገኙ “49 የተከበሩ የምክር ቤት አባላት” የት ነበሩ? እነማንስ ናቸው? የዜጎቻችን ህይወት እናስቀጥል ወይስ አናስቀጥል? ከሚል አጀንዳ በላይስ ምን የህዝብ የሆነ ታላቅ አገራዊ ጉዳይ ገጠማቸው? መመለስ ያለበት ይህም ነው።

ይህን መልስ በዋናነት መመለስ ያለበት እንደ ድርጅት የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ፣ የህዝብ ወኪል እንደመሆንና አሰራርን እንደማክበር ደግሞ ራሱ የተከበረው ምክር ቤት ነው። አለበለዚያ ኢህአዴግ በተመረጠበት ህዝባዊ አጀንዳ አስፈፃሚውን በመቆጣጠርና በመከታተል፣ የህዝቡን ደህንነት በመጠበቅና መደበኛ ህይወቱን የተሻለ ለማድረግ በመከታተል፣ እንደ አስፈፃሚም በተቋማት በኩል ለዜጎች በሚሰጥ አገልግሎት አመርቂ ስራ በማቅረብ ብቻ ሳይሆን ተከታይ በማፍራት፣ በመምራትና በመታመን ወዘተ…ለህዝብ አሳካዋለሁ ብሎ ቃል የገባው ጉዳይ ከባድ አደጋ ይገጥመዋል። እነሆ… ስለምክር ቤቱ፣

ከቅርብ ምንጮች እንደተገኘው መረጃ ከሆነ ከምክር ቤቱ 547 አባላት 8 ሰው በአሳማኝ ምክንያት አልተገኘም (በህመምና በሞት)። በዚህም ምክንያት በምክር ቤቱ መገኘት የነበረባቸው 539 አባላት ሲሆኑ የተገኙት አባላት ግን 490 (ምክር ቤቱም ይህን ቁጥር በአግባቡ በመግለፅ በኩል የፈጠረው ክፍተት እንዳለ ሆኖ) ናቸው።

ቀሪዎቹ 49 አባላት ከዚህ ትልቅ አገራዊና ህዝባዊ አጀንዳ በላይ ምን ገጥሟቸው ይሆን? ይሄ የማያወላዳ ምላሽ ያሻዋል። አሳማኝ ምላሽ ካላገኘና በኢህአዴግ ውስጥ በዚህ ዙሪያ መተማመን ካልተፈጠረ በተሃድሶ ጉዳይ ላይ ለራሱ ትልቁን የቤት ስራ ወስዶ ያለ እረፍት በመስራት ህዝብና አገር እየለወጠ ያለው ኢህአዴግ ፈተና ይገጥመዋል። በእርግጥ ለፈተናና ለመፍትሄ አዲስ ያልሆነው ኢህአዴግ ይህን ፈተና አሸ/ቸ/ንፎት እንደሚያልፈው ጥርጥር የለውም።

ነገር ግን በዚህ ትልቅ ወሳኝ ጉዳይ (ፅንፈኛው፣ የአገራችንን የህዳሴ ጉዞ ለማደናቀፍ የሚሰው የውስጥና የውጭ ሃይል፣ ለህዝብ ታማኝ ያልሆነው ተቃዋሚ ወዘተ…) ከኢህአዴግ ጋር ፊት ለፊት እየተዋጋ ባለበት ወቅት ከወሳኙ የአስተሳሰብ ፍልሚያ ራሳቸውን የደበቁ በከፍተኛ የመንግስትና የድርጅት ስልጣን ላይ ያሉ ሰዎች ለምን አፈገፈጉ? ለምንስ የሌሊት ወፍ መሆን መረጡ? ብሎ መመልከት ያስፈልጋል።

በእነዚህ ወገኖች ጉዳይ የታየው ህመም የፖለቲካ ግንባታ ጉድለት እንዳለው ሆኖ የአጠቃላዩ ኢህአዴግ ጉድለት ተደርጎ መወሰድ አይኖርበትም። ነገር ግን ወትሮ በተለያዩ አጋጣሚዎችና ክስተቶች ስለኢህአዴግ ከእኔ በላይ ለአሳር የሚሉትን ጨምሮ በመንግስት ጉዳይ ብዙ ሲነግሩን የነበሩ ጓዶች በእንዲህ አይነቱ ወቅት ምን በልጦባቸው ይሆን? ምንስ ጎተቶአቸው ይሆን? የትኛው ጉዳይ አጓጉቷቸው ይሆን? ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል።

ለእኔ ከእነሱ ይልቅ፣ ይሳሳቱም አይሳሳቱ በመድረኩ ተገኝተው አቋማቸውን ያራመዱ የመስመር ከሃዲዎች ይሻላሉ። ከሃዲዎች የምልበት ምክንያት የተመረጡበትን ፕሮግራምና የወከሉትን ኢህአዴግ ቅርጥፍ አድርገው ስለካዱት ነው። በሌላ አነጋገር ኢህአዴግ ናቸው ብሎ የመረጣቸውን ህዝብ ካርድ ዋጋ ቢስ ስላደረጉትና የምክር ቤቱን አሰራር ስለጣሱም ነው።

ከላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ እንደ ሌሊት ወፍ ራሳቸውን ይዘው ከፊት ለፊቱ ግንባር የተሰወሩት ጓዶች፣ ለአንድ በህዝብ የተመረጠ የኢህአዴግ ምክር ቤት አባል ለተመረጠበት ፕሮግራም ከመታመን በላይ፣ አሰራሩን ካላመነበትም ራሱን ከመረጠው ድርጅት ከማግለል በላይ ቀላል የሆነ ነገር እያቻሉ፣ ለፕሮግራሙ መሳካት መስዋዕትነት ለመክፈል ተዘጋጅቼያለሁ ሲሉ እንዳልማሉ ሁሉ መሃላውን በአደባባይ መብላታቸውን አሳይተውናል። ይሄ ትልቅ የሰብዕና ውርደትም ጭምር ነው።

እነዚህ ሰዎች ራሳቸውን የኢህአዴግን መርህና አሰራር ለሚያውቅ ከተራ አባል ጀምሮ ላለ የድርጅቱ አባል እነዚህ ሰዎች ፈፅሞ አርአያ ሊሆኑ የማይችሉ፣ አባሉ ከሚከተላቸው ይልቅ እንዲያፍርባቸው የሚያደርጉ፣ የኢህአዴግን ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት አምነው ያስፈፅማሉ ተብሎ እምነት የማይጣልባቸው ሆኖ እንዲታዩ አድርገዋል። በስራ እርከኖቻቸው የሚሰጧቸውን መመሪያዎች በእርግጥ አምነውባቸው ነው ሊያሰኝ የሚችል ጥርጣሬም ፈጥረዋል።

የትላንቱን የምክር ቤት መድረክ ለተከታተለ ለእንደ እኔ አይነቱ ሰው፣ ሁልጊዜም የግንባር ስጋ በሚሆኑት የኢህአዴግ አመራሮችና አባላት ይኮራል። ከጀርባቸው ስንት አይነት ስም እየተሰጣቸው ለቆሙለት ህዝብና ዓላማቸውን ለሚደግፈው ማህበረሰብ ማንነታቸውን፣ ስማቸውንና ጊዜያቸውን ሰጥተው ሁሉንም መስዋዕትነት ሲቀበሉ ማየት በእርግጥም ያኮራል። እነዚህ ጓዶች ስልጣንን በሞቀበት እየሞቁበት ሳይሆን የህዝብ ሰላም፣ ደህንነትና ዘላቂ ጥቅም ማስከበሪያ አድርገው አሳይተውናል። ላመኑበት ዓላማ ሲያዘነብል ጎድለው ሳይሆን፣ ባሉበት ፀንተው ህዝባዊነትን አመላክተውናል።

በዚህም ምክንያት የፓርላማው ውሎ የአገራችን ህዝቦች እውነቱ የቱ ጋር እንዳለና የቱ እንደሚጠቅመን በግላጭ እንዲመለከቱና እንዲመረምሩ አስችሏል። በእርግጥም እንዲህ አይነት ያልተጠበቀ ክስተት መታየቱ የከፋው መደበላለቅ እንዳይኖር የሚያደርግ፣ ለበለጠ ህዝባዊነት የሚያግዝ ምርጥ አጋጣሚም ነው።

በአንፃሩ በዚህ ህዝባዊ አጀንዳና አገር ትቀጥል አትቀጥል በሚል ድምፀ ውሳኔ ከፊት መምጣት ተስኗቸው በቆሙበት የተንሸራተቱ፣ መጣሁ ብለው የጠፉ በስም ከፍታቸው ልክ በግብራቸው ያልታዩትንም ታዝበናል። ለእነዚህ ኢህአዴግ መፍትሄ ይስጣቸው እንጂ ህዝቡማ ታዝቧቸዋል።

አንዳንዶች ይህን የፓርላማ ትዕይንትና የመገኘት ያለመገኘት ጉዳይ ከሃሳብ ነፃነትና ዴሞክራሲ መብት ጋር አያይዛችሁ ልታዩት እንደማይገባ ለማሳሰብ፣ የየትኛውም አገርና መንግስት ተወካይ እቆምለታለሁ ብሎ በተመረጠበትና ቃል በገባለት ህዝብና ዓላማ ጉዳይ አይደራደርም። ከውግንናውን ለአፍታ አይወላውልም።

እንደ ጃዋር አይነቱ ጠባብና የብተና አቀንቃኝ የመረጠውንና የወከለውን ህዝብ በማዋረድ፣ የኮሮጆ ሌባ ብሎ በመሳደብ ህዝቡ ላይ ንቀት ማሳደሩና መልሶ ህዝቡን አደጋ ላይ መጣሉ ሳያንገበግበው በተቃራኒ የቆመለትን የዴሞክራሲና የልማት ፍላጎት ተቃርኖ መቆም ወይም ከትግል ማፈግፈግ በፍፁም ዴሞክራሲያዊ አያሰኝም።

ስልጣን የህዝብ መሆኑን ያመነ አመራር፣ ይህንንም አምኖ በጋራ አሰራር ለመፈፀምና ለማስፈፀም ቃል የገባ አመራር የአየር ሁኔታውን እያየ አይታገልም። እንዲያ ከሆነ ትግሉ ለራሱ ጥቅምና ለመቀመጫው ነበር። እንዲያ ከሆነ፣ ለመስመር ሳይሆን ግለሰብ ያሾረው የነበረ ቡድንተኛም ነበር። እንዲያ ከሆነ አሁንም ኢህአዴግ ሆኖ የሚመራበት ሞራልና አቋም ይዞ ሊቀጥል አይችልም።

ስለዚህም ኢህአዴግ በብርቱ ራሱን ከእንክርዳዱ መለየት ያለበት አሁን ነው። ኢህአዴግ ሆኖ እንክርዳድ መሆን እንደማይቻል በግላጭና በፍጥነት ማረጋገጥ ያለበት አሁን ነው። በተለይ በዚህ ወቅት ህዝቡና ራሱ የኢህአዴግ አመራሩና አባሉ በሚያስደነግጥ ሁኔታ በበቂ መጠን ግንዛቤ ስላገኘና ስለተገነዘበ ከጎኑ እንደሚቆም ጥርጥር የለውም።

የኢህአዴግ ሌላው እድል፣ ድርጅቱ ራሱ ከማንም በፊት የጎራ መደበላለቅና ስልጣንን ለህዝብ ጥቅም ማዋል ላይ ሰፊ ችግር አለ ብሎ ሰለገመገመ፣ ይህን ሀቅና እውነታ በግላጭ ህዝቡ ጭምር ማረጋገጡ ለቀጣዩ ተሃድሶውና የድርጅቱ ጥራት ሰፊ እድል የሚፈጥር ነው። የድርጅቱን ዴሞክራሲያዊነትም በዚያው ልክ የሚያረጋግጥ ነው። ነገር ግን አሁንም ኢህአዴግ በእኔ መስመር ኢህአዴግና እንክርዳድ ሆኖ መቀጠል አይቻልም። ይልቁንም ሳይውል ሳያድር የመንሸራተት ሀይሉን ጎራህን ለይ ሊለው ይገባል።